<u>መመሪያ፡-</u>

- *መመሪያዎቹን በጥንቃቄ አንብቡ። ስለ ፈተናው ጥያቄ ካላችሁ ፈተናው ከመጀመሩ በፊት ፈታኙን /ፈታኟን መጠየቅ ትችላላችሁ። ፈተናው ከተጀመረ በኃላ ምንም ዓይነት ጥያቄ መጠየቅ አይቻልም።*
- *ይህ የአማርኛ ትምህርት ፈተና ነው ። የጥያቄው ብዛት 40 ጥያቄዎች ሲሆኑ የተሰጠው ጊዜ 1 ሰዓት ሲሆን ከአንድ ሰዓት በላይ መስራት አይፈቀድም ።*
- *ከተፈቀደው ጊዜ ቀድማችሁ ከጨረሳችሁ የሰራችሁን ፈተና በድጋሚ መፈተሽ ወይም ማረጋገጥ ትችላላችሁ። እያንዳንዱ ጥያቄ አራት አማራጮች አሉት ጥያቄዎቹንና ምርጫዎቹን በጥንቃቄ ካነበባችሁ በኃላ መልሳችሁን በሚሰጣችሁ የመልስ ወረቀት ላይ ፃፉ።*
- *መልሶቻችሁን ለመፃፍ ከምርጫችሁ ስር የሚገኘውን ሳጥን አጥቁሩ ወይም አቅልሙ።*

ለምሳሌ፡-መልሳችሁ ሁለተኛ ምርጫ ከሆነ ከስሩ የሚገኘው ሳጥን ውስጥ ከዚህ በታች በቀረበው መልክ አጥቁሩ

ሀ	ለ	ሐ	መ
☐	☐	☐	☐

- *ፈተናውን ለብቻችሁ መስራት ይኖርባችኃል። በማንኛውም መንገድ ለማጭበርበር ከሞከራችሁ ውጤታችሁ ወይም ድካማችሁ ዋጋ ያጣል።*

መመሪያ አንድ ፦ ከተራ ቁጥር **1-10** ድረስ ያሉ ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ የተመሰረቱ ናቸው። ምንባቡን በጥሞና በማንበብ ጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ ምርጥ/ምረጡ።

ምንባብ

እሁድ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት 2000 ዓ.ም በደቡብ የኢትዮጵያ ክፍል ከጅንካ ሃያ ኪ.ሜ ወጣ ብሎ ቃቆ የምትባል ቦታ ላይ ከምድር እኩል የተፈጠረውን ንፁህ አየር ይኸውልሽ አለ ጋሻው የወንዘቹን አወራረድ እንደጥላ የምትከተለውን ሃናን እያየ። እንዴት ደስ ይላል! የተራራው አቀማመጥ የዛፎች አቋቋም አለች ዙርያ ገባውን እየተመለከተች።

በዚህ ቃቆ የምትባል አካባቢ በነ የሚባል የንሳ መጠሪያ ያላቸው ኢትዮጵያን ይኖራሉ። ወዲያ ማዶ ደግሞ ማሊ የሚባሉ አሉ።ታድያ የሁለቱም ጎሳ አባላት ልብስ የሚባል ነገር አያወቁም። እንዲያው ሃፍረታቸውን ለመሸፈን ያህል ትንሽዬ ቆዳ ያንጠለጥላሉ። ከቡስካ በስተጀርባ የተባለው መፅሐፍ ውስጥ እንዳሉት ሐመሮች።

''አንብበሽዋልን?''

''እንዴ? ለዛውም ደጋግሜ ነዋ''

''ብራቦ ሃኒ''

ረጅሙን የዙም ሌንስ በዘመናዊ ካሜራው ላይ እየገጠመ "አሁን እስከ ሁለት ኪ.ሜ ርቀት ድረስ ማንሳት እችላለሁ" አላት በጣም ተደንቀች። ወንዙ ዳር ያለችው ዛፍ ላይ ወጠና ወዲያ ማዶ ደን ላይ አነጣጣረ ምንም የለም ወዲህ አነጣጣረ እንዲዚያው ዱብ ብሎ ወረደ። በዛፉ ቅጠላቅጠል መሃል እየተሸሎከለኩ በሳቅ እየተፍነከነኩ አንድ ገለጣ ቦታ ብቅ አሉ። እፍረቷ አካባቢ ብቻ ሦስት ማዕዘን ቁርበት ጣል አደረገች የበና ልጃገርድ ጋር ተፋጠጡ። ደንግጣ እንደሃውልት ድርቅ አለች።የበናዋ ቆንጆ ጡቶቿ ለመተኮስ የተወደሩ ሮኬቶች ይመስላሉ። በቀይ አፈር የታሸው ፀጉርዋ ቁልቁል ይጥመዘመዛል። ከቀላጭ ብረት የተሰሩ ሦስት ቀለበቶች በአንገቷ ዙሪያ ተጠምጥመዋል። ሃና አፏን ከፍተች። የበነዋ ቆንጆ ተክለ ሰውነት ትንግርት ሆኖባታል። የአካላቷ ጥብቀት፤ ወሂና ጠይምነቷ ወከከ ያደርጋል።

ጋሻው ቀስ ብሎ ጣቶቹን ከካሜራው ጋር አገናኘ። ልጅ እገረዲቱ ሃናን በአይኖቹ ወጋቻት።ጆሮቹም ትልልቅ ሎረዋችን አንጠልጥለዋል።ከንዷም ከላይ እስከታች በመደብና ቀላጭ ብረቶች አጊጠዋል። የጋሻው የሃናና የበናዋ ጉብል የልብ ትርታ ቆሚል።የዓይን ርግብግብት ሳይቀር ተቋርጧል። የበናዋ ቆንጆ ፊት ላይ ቁጣ ድፍረትና ግርምት ይነባባል። ጋሻው ካሜራውን ዓይኑ ላይ ሳያደርግ በግምት ማንሳት ተከኗል። የበናዋ ጉብል አፈገፈገች የሃና ዓይኖች ልጅ አገረዲቱ ባዶ እግሮች ላይ አረፈ። አልቦዋቿ አንፀባርቁባት ጉብሊቱ አፈገፈገች። ጋሻው የካሜራው መምቻ ተጫነ ቀጥ ቱር አለች እንደሚዳቋ። ጋሻው ዘሎ ከፍታ ላይ ወጣ። ካሜራው አይኑ ላይ ነው።በሌንሱ ውስጥ የጉቢሊቱ ምስል ይረመስመሳል። ከምን ይላል ጋሻው ሌንስን ዞር ቀጥ ዞር ቀጥ በተከታታይ የካሜራውን መምች ተጫነው ፈልሙ ሲያልቅ ቆመ። በፍጥነት ቀይሮ አነጣጠረ የበናዋ ቆንጆ የለችም። በመጪው ዓመት ካናዳ ቀሮንቶ ውስጥ የሚካሄደውን አለም አቀፍ የፎቶግራፍ ውድድር አሸናፊነቱን ደመነፍሱ ከወዲሁ ሹክ አለው።ምንጭ ልዑል ግርማ 2000 ለማሸነፍ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር የሥንጽሁፍ ፀሎት ብሌን 3 ገፅ 16

----------1. በምንባቡ ውስጥ ጋሻው የተባለው ተጠቃሽ የፎቶ ማንሳት ተግባሩን የሚፈፅመው የት ቦታ ነው?

ሀ. ቡሳካ ሐ. ቃቆ

ለ. ማሊ መ. በነ

--------2. በአንቀፅ አንድ ላይ በማወዳደር የቀረቡት እነማን ናቸው?

ሀ. ጥላና ሃና ሐ. ቡስካና ቃቆ

ለ. በነና ማሊ መ. ቆንጆዋና ሚዳቆዋ

--------3. በጽሁፍ ውስጥ የተገለፀው ገፅ ባህሪ ካሜራውን ለማንሳት ያስተካከለው ለስንት ኪሎ ሜትር ነው ? /አንቀፅ ሶስት/

ሀ. አንድ ኪሎ ሜትር ሐ. መቶ ሜትር

ለ. ሶስት ኪሎ ሜትር መ. ሁለት ኪሎ ሜትር

-------4. "የአለም አቀፍ የፎቶ ግራፍ ውድድር አሸናፊነቱ ደመነፍስ እንደሆነበት" የተገለፀው በአንቀፅ ስንት ነው?

ሀ. አንቀፅ አራት ሐ. አንቀፅ ሁለት

ለ. አንቀፅ አንድ መ. አንቀፅ ሶስት

-------5. በአንቀፅ ሁለት ላይ "እንዲያው <u>ሃፊረታቸውን ለመሸፈን</u>" በሚለው የተሰመረበት ሀረግ ፍቺ -------ነው።

ሀ. ፍርሃት ሐ. የመራቢያ አካላት

ለ. የተለመደ የአካል ክፍል መ. እጅና እግር

-------6. በአንቀፅ ሶስት ላይ "ሶስት ማዕዘን <u>ቁርበት</u> ጣል ካደረገችው" በሚለው ውስጥ የተሰመረበት ቃል ተመሳሳይ ፍቺ -------- ነው።

ሀ. የቆዳ ውጤት ሐ. የላስቲክ ውጤት

ለ. የጥጥ ውጤት መ. የእንጨት ውጤት

-------7. በአንቀፅ አንድ ላይ ፀሃፊው የወንዙ አወራረድ የተራራው አቀማመጥ አለች <u>ዙሪያ ገባውን</u> እየተመለከተች በሚለው ሃረግ ውስጥ የተሰመረበት ምንን ይገልፃል?

ሀ. የሚወጣውን ሐ. የሚሸከረከውን

ለ. የሚገባውን መ. አካባቢውን

-------8. በአንቀፅ ሶስት ላይ "የአካሏ ጥብቀት፤ ወዟን ጠፅምኒቷ ወከክ ያደርጋል" ። በሚለው አ.ነገር ውስጥ <u>ወከክ</u> የሚለው የሚገልፀው ------ነው?

ሀ. መከፍትን ሐ. መቆጣትን

ለ. መማርከን መ. መጋራትን

------9. በአንቀፅ አራት ላይ <u>ጉበሊቱ</u> ተብላ የተገለፀችው ማን ናት ?

ሀ. ሃና ሐ. የበነዋ ቆንጆ

ለ. ስፈሩ መ. የሚሊ ቆንጆ

--------10. በአንቀፅ ሶስት ላይ ፀሃፊው <u>"ለመተኮስ የተወደሩ ሮኬቶች</u>" ሲል -----ማለቱ ነው ?

ሀ. የተጋደሙ ሐ. የተንጋደዱ

ለ. የቆሙ መ. የተዘቀዘቁ

<u>መመርያ ሁለት፦ ከዚህ በታች የቀረቡት የተለያዩ ይዘት ያላቸው ጥያቄዎች ናቸው። ለጥያቄዎቹ አራት አራት አማራጭ መልሶች ተሰጥተዋል። ይበልጥ ትክክለኛ መልስ የያውን ፊደል በመልስ ወርቀቱ ላይ አስፍሩ።</u>

--------11. ከሚከተሉት ውስጥ መልዕክትን ለመቀበል ወይም ተቀባይ ክሂል የሆኑት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ማደመጥና ማንበብ ሐ. ማዳመጥና መናገር

ለ. መፃፍና ማንበብ መ. ማንበብና መፃፍ

-------12. ከቀረቡት ዓ.ነገሮች ውስጥ የትንቢት ጊዜ የሚገልፀው የትኛው ነው?

ሀ. ታምረናል ሐ. እየተማረን

ለ. እንማራለን መ. ስለተማርን

-------13. አንድን ምንባብ በፍጥነት በማንበብ ምንባቡ ጠቃሚ መሆኑን አለመሆኑን የምናውቅበት የንባብ ስልት ----------ነው።

ሀ. አስሳ ንባብ ሐ. ገርፍ ገርፍ ንባብ

ለ. ስፊ ንባብ መ. ጥልቅ ንባብ

-------14. በአንድ ጽሁፍ ውስጥ ከመጀመሪያ ሆነ ከመጨረሻ ተጓርዶ የቀረበ ሃሳብ መኖሩን የሚያመላክተው ስርዓተ ነጥብ የቱ ነው ?

ሀ. ትዕምርተ ጥቅስ ሐ. ቅንፍ

ለ. ነጠብጣብ መ. ጭረት

-------15. የሆህያት ስርዓታዊ ቅንጅት ሆኖ፤ትርጉም ያለው ወደ አነስተኛ ቅንጣት ሊሸነሸን የማይችል የቋንቋ መዋቅር የቱ ነው ?

ሀ. ድምፅ ሐ. ዓ.ነገር

ለ. ቃል መ. ምዕላድ

-------16. ስለ አንቀፅ ምንነት ትክክል <u>ያልሆነው</u> የቱ ነው ?

ሀ. ተያያዥነት ያላቸው ዓ.ነገሮች ቆንጅት ሐ. አንድ ፍሬ ሃሳብ ያለው

ለ. የጽሁፍ አካል ያልሆነ የዓ.ነገር ሰብሰብ መ. ልብ ወለድና ኢ. ልብወለዳዊ ሀሳብ የሚፃፍበት

-------17. ስለ ስም የቃል ክፍል ትክክል <u>የሆነው</u> የቱ ነው?

ሀ. የባለቤትነት አገልግሎት ያለው ሐ. አብዥ ቅጥያ የማይወስዱ

ለ. በዓ.ነገር መጨረሻ ብዙ ጊዜ የሚገባ መ. ኡና-ኤጥገኛ ምዕላድ የማይቀጠልበት

-------18. መሰረት ክፍኛ ታመመች።በሚለው ዓ.ነገር ውስጥ ተወስከ ግሱ የትኛው ነው?

ሀ. መሰረት ሐ. ታመመች

ለ. ክፍኛ መ. ክፍኛ ታመመች

------19. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛ ምዕላዳዊ አተናተን ስርዓት የሚይታይበት የቱ ነው?

ሀ. የወንድሞቼ-ን ሐ. የ-ቤተሰብ ኦች-ኣችን

ለ. ስለ-መለከታዊ -ነት -ኡ መ. የቤተሰብ-ኦች-ኡ

-------20. ከሚከተሉት አማራጮች መካከል በፊደል ገበታ ስርዓት ቀድሞ የሚገኘው የቱ ነው?

ሀ. ዝናብ ሐ. ዓለም

ለ. ደመና መ. ሽመና

-------21. ከቀረቡት ቃላት መካከል ጥምር የሆነው ቃል ---------ነው?

ሀ. ስነ ምህዳር ሐ. ሰፊ መንገድ

ለ. የአመጋገብ ስርዓት መ. ኑሮና ጊዜ

--------22. ሐረግ መዘዘ ሲል --------ማለቱ ነው?

ሀ. ታሪክ አቀረበ ሐ. ህግ ነገረ

ለ. ምክር ሃሳብ ሰጠ መ. ዘር ቆጠረ

------23. ከሚከተሉት ውስጥ የወል ስም መጠሪያ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. አበበ ሐ. አባይ

ለ. እንስሳት መ. ሞገስ

------24. ምዕላዶች ካላቸው አገልግሎት አንፃር በስንት ይከፈላሉ?

ሀ. በአራት ሐ. በአምስት

ለ. በሁለት መ. በሦስት

-------25. ደስታ ብሎ "ሀዘን" ካለ "ፍቅር" ብሎ -----ይላል።

ሀ. ጥላቻ ሐ. መፍቀር

ለ. መምድድ መ. መከራ

-------26. "ዘወትር" ብሎ "ሁል ጊዜ ቢል "የላቀ" ብሎ ------ይላል።

ሀ. ትንሽ ሐ. ያነሰ

ለ. የተለቀቀ መ. የበለጠ

------27. በአንድ አንቀፅ ውስጥ ዋናውን ሐሳብ የሚይዘው ክፍል -------ይባላል።

ሀ. መዘርዝር ሐ. ሀይለቃል

ለ. ዋና ዓ.ነገር መ. ለ ና ሐ

------28. ከፍተኛ ድምፅና አካላዊ እንቅስቃሴ የሚጠይቀው የሥነ ቃል ዓይነት የቱ ነው ?

ሀ. ፉከራ ሐ. ተረትተረት

ለ. እንቆቅልሽ መ. አፈታሪክ

-------29. ከሚከተሉት ውስጥ የጊዜ አመልካች ተውሰ ከግስ <u>ያልሆነው</u> የቱ ነው።

ሀ. አሁን ሐ. ትናንት

ለ. በኃላ መ. ሁኔታ

------30. በዚህ ወር እኛ ሚኒስትሪ ፈተና እንፈተናለን በዚህ ዓ.ነገር ውስጥ ያለው የጊዜ ዓይነት የቱ ነው?

ሀ. የወደፊት ጊዜ ሐ. የሀላፊ ጊዜ

ለ. የአሁን ጊዜ መ. የቅርብ አሁን ጊዜ

-------31. የተውሳካ ግስ አገልግሎት ምንድ ነው?

ሀ. ግሱን ከጊዜ ከቦታ ከሁኔታ አንፃር መግለፁ ሐ. የዓ.ነገር ባለቤት ሆኖ ማገልገል

ለ. ከግሱ ውጪ ያለውን ባለቤት መግለፅ መ. የዓ.ነገር መዝጊያ በመሆን የሚያገለግል

------32. ናቸው ሴቶች የስድስተኛ መምህራኖች አማርኛ ክፍል ። ይህ ዓ/ነገር ተስተካከሉ ሲባፍ

ሀ. አማርኛ መምህራኖች ሴቶች ናቸው ስድስተኛ ክፍል።

ለ. የስድስተኛ ክፍል አማርኛ መምህራኖች ሴቶች ናቸው።

ሐ. ሴቶች መምህራኖች ናቸው የስድስተኛ ክፍል

መ. የስድስተኛ አማርኛ ክፍል ሴቶች ናቸው

------33. ስለአመዘዘኝ ድርሰት ትክክል <u>የሆነው</u> የቱ ነው ?

ሀ. ሁለት ነገሮችን እያወዳደረና እያነፃፀር ይፃፈል

ለ. ነገሮችን በመግለፅና በማብራራት ይፃፉል

ሐ. ታሪኮችን በቀደም ተከተል ይፃፉል

መ. በቃላት ምስል በመከሰት ይፃፉል

-------34. የአንድ ቃል ቀጥተኛ ወይም መዝገበ በቃላዊ ፍቺ ----ተብሎ ይጠራል

ሀ. ፍከሬያዊ ፍቺ ሐ. ፈለጠዊ ፍቺ

ለ. እማሬያዊ ፍቺ መ. ተቃራኒ ፍቺ

------35. ምሁር ለሚለው ይበልጥ ቀረቢ ፍቺ የሚሆነው የቱ ነው ?

ሀ. የቀለም ቀንድ ሐ. ዋንጫ

ለ. ብሄር መ. ቀለም

------36. አስቴር <u>ሩሀሩህ</u> ልጅ ነች የተሰመረበት ቃል ምንን ያመለክታል?

ሀ. ቀለምን ሐ. መጠንን

ለ. መልክን መ. ሁኔታን

------37 ከሚከተሉት ገላጮች መጠንን የሚያመለክተው የቱ ነው ?

ሀ. አጭር ሐ. ክፉ

ለ. ቀይ መ. ቆንጆ

-----38. ከሚከተሉት ቃላት ቅድመ ግንድ ቅጥያ ያለው ቃል የቱ ነው ?

ሀ. መፀሐፍን ሐ. ሰባበረ

ለ. ስለፍቅር መ. ቤታችን

------39. ከሚከተሉት ውስጥ የድርሰት ክፍል <u>ያልሆነው</u> የቱ ነው ?

ሀ. መግቢያ ሐ. ሐተታ

ለ. ንፅፅር መ. መደምደሚያ

------40. በአንድ አንቀፀ ውስጥ ስንት ዋና ሐሳብ ሊኖር ይችላል?

ሀ. ከአንድ በላይ ሐ. ሁለት

ለ. አንድ መ. ከሁለት በላይ

የወረዳ 9 ትምህርት ጽ/ቤት ክለስተራዊ አማርኛ ትምህርት የ 2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን የመጀመሪያ ሴሚስተር ሞዴል ፈተና መልሶች።

- **<u>የምንባብ ጥያቄዎች መልስ</u>**

1. ሐ
2. ሀ
3. መ
4. ሀ
5. ሐ
6. ሀ
7. መ
8. ለ
9. ሐ
10. ለ

<u>የይዘትና ልዩ ልዩ ጥያቄዎች መልስ</u>

11. ሀ
12. ለ
13. ሐ
14. ለ
15. መ
16. ለ
17. ሀ
18. ለ
19. ሐ
20. መ
21. ሀ
22. መ
23. ለ
24. ለ
25. ሀ
26. መ
27. መ
28. ሀ
29. መ
30. ሀ
31. ሀ
32. ለ
33. ሀ
34. ለ
35. ሀ
36. መ
37. ሀ
38. ለ
39. ለ
40. ለ